የውስጥ መግለጫ

722/2013

26

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
Ministry of Urban Development and Construction

ለ፡ አዲት መምሪያ

ለ፡ ህግ መምሪያ

ከ፡ ሀብት ሥራ አመራር ማስተባበሪያ ቢሮ

ቀን ፡ መስከረም 3 ቀን 2006 ዓ/ም

ከበደ ብዙ
የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ
ኃላፊ

ጉዳዩ፡- <u>የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣</u>

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 26/2005 ሆኖ ከጳጉሜን 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል።

በዚህ መሰረት መመሪያውን እንድናስፈጽም በቁጥር 252መ250/39 ጳጉሜ 5 ቀን 2005 ዓ/ም በተላፈ ደብዳቤ 1 ጥራዝ ሰነድ ተልኮልናል። ለአሰራር እንዲረዳችሁ የጥራዙን ኮፒ ከዚህ ማስታወሻ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለፋይናንስ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
ከ.ል.ኮ.ማ/ር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

ቁጥር Ref.No. ኢ.ፌ.ዲ.ሪ 25262252/39
ቀን Date. 5/13/2801

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

ለሃብት ሥራ አመራርና ማስተባበሪያ ቢሮ
ኦ/ል/ኮ/ሚ/ር፣

ጉዳዩ፡- **የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣**

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 26/2005 ሆኖ ከጳጉሜን 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሰረት መመሪያውን እንድታስፈጽሙ የጸደቀው 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድትከታተሉት እናሳስባለን።

ክፍለማሪያም ገ/ር
መሪ ጋይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለሚኒስቴር ጽ/ቤት እና ሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለ5ኛው የከተሞች ሣምንት አብይ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሣምንት የቴክኒክ ኮሚቴ
- ለፋይናንስ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
  ኦ/ል/ኮ/ሚ/ር፣

ስልክ/ Tel.
011-553-16-88
011-553-16-72
011-553-16-73

ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
24134/1000

ፋክስ /Fax
011-554-12-68

ድህረ ገጽ / Web Site
WWW.mudc.Gov.et
E-Mail: mwud_sm@ethionet.et

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት
ETHIOPIAN CITIES WEEK

Ethiopian Cities Network

Bahir Dar

5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 722/2013

ጳጉሜን 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ ገፅ

1. መግቢያ 2
2. አጭር ርዕስ 3
3. ትርጓሜ 3
4. የመመሪያው ዓላማ 3
5. የፋይናንስ መመሪያ መርሆዎች 3
6. ባህር ዳር የሚተላለፈውን የሥራ ማስኬጃ ሂሣብ በተመለከተ፤ 6
7. የግዢ መመሪያ መርሆዎች፤ 7
8. የፋይናንስና የሎጀስቲክስ አቅርቦት ሥራዎች የሚያስተባብር ኮሚቴ፤ 9
9. የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች፤ 9
10. የቢሮ ዝግጅት፤ 10
11. የመመዝገቢያ ክፍያ፤ 10
12. የኤግዚብሽን ቦታ /ድንኳን/ ኪራይ አከፋፈል፤ 10
13. ከእስፖንሰሮች የሚገኝ ገቢን በተመለከተ፤ 11
14. ሂሣብ ማስመርመር፤ 11
15. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ፤ 11

መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ አመታዊ የከተሞች ሳምንት የተሰየመ ሲሆን፤ በዚሁም መነሻነት ቀደም ሲል እንደኛው፣ ሁለተኛው፣ ሶስተኛው እና አራተኛው የከተሞች ሳምንት በተለያዩ ከተሞች የተካሄደ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ 5ኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት በባህር ዳር ከተማ ከህዳር 11- 17 ቀን 2005 ዓ.ም ይከበራል::

እንደሚታወቀው ማንኛውም ተቋም የተሰጠውን ተግባርና የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ ሊያከናውን የሚችለው የተጠናከረ የገቢ ምንጭና በትክክል የተደራጀ የፋይናንስና አቅርቦት አመራር ስልት ሲኖረው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም:: የተደራጀና የተጠናከረ የፋይናንስና አቅርቦት አመራር ሲባል አንድ ተቋም የሚሰበስበውን ገቢ፣ የሚያወጣውን ወጪና አቅርቦት እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውለው የሚከተለው የአሠራር ስልት ማለት ነው:: ለዚህም የፋይናንስ ዕቅድና የፋይናንስ አያያዝ መመሪያዎችን እንዲሁም የአቅርቦት አፈጻፀም መመሪያ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ አመቺ ስልት መቀየስ፣ የተሟላና ተገቢ ይሆን የሒሳብና የአቅርቦት መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል::

ስለሆነም 5ኛውን የኢትዮጵያ የከተሞች ሳምንት ዝግጅት በአግባቡ ለማካሄድ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በኃላፊነት እንዲመራ የተደራጀ ኮሚቴና የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ሥራቸውን ሲያከናውኑ የሚፈለግባቸውን ተግባር ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል:: ከዚህ አኳያ የሚያከናውኑትን የዕለት ተዕለት ሥራ በአግባቡ ለማከናወን የሚረዳ የፋይናንስና ሎጂስቲክ የአቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ሊኖር ይገባል:: በዚህም መሠረት ይህ አጭር የፋይናንስና ሎጂስቲክ የአቅርቦት አሠራር መመሪያ ተዘጋጅቷል::

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የአምስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የፋይናንስና የሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 722/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ገቢ/መዋጮ" ማለት ለአምስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ዝግጅት ማከናወኛ ከመመዝገቢያ፣ ከድንኳን ኪራይ፣ ከስፖንሰሮች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሰበሰብ ነው።

2) "ወጪ" ማለት ከአምስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ሥራ ጋር በተገናኘ በተገቢው አካል ሲፈቀድ የሚፈፀም ክፍያ ነው።

3) "ከተማ አስተዳደር" ማለት አምስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ላይ የሚሳተፉ ከተሞች ናቸው።

4) "የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር" የአምስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት እንዲያስተናግድ የተመረጠ ከተማ ነው።

5) "አቅርቦት" ማለት ለአምስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት በዓል አከባበር የሚውል ማንኛውም አይነት በግዥ፣ በስጦታ እና በትውስት የሚቀርብ ቁሳቁስ እና እገልግሎት አቅርቦት ነው።

3. **የመመሪያው ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የአምስተኛውን የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ግዥ ለመፈፀም፣ በአግባቡ ክፍያ ለመፈፀም፣ ተገቢውን ምዘጋባ በማካሄድ ሂሣቡን ለማስመርመር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ነው።

4. **የፋይናንስ መመሪያ መርሆዎች**

1) ተቀባይነት ባላቸው የፋይናንስ አሠራር መርሆዎች፣ በሕግና በመንግሥት መመሪያዎች መሠረት ከኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት አከባበር ጋር በተያያዘ ያለውን ሂሣብ መዝግቦ በአግባቡ መያዝ፣ ገቢዎችን መሰብሰብ እና በጥንቃቄ እንዲያዝ ማድረግና ወጪዎችን መክፈል፣ ለሦስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች የሚውሉ መደበኛና ልዩ የሒሳብ መግለጫ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና ማስመርመር ከፋይናንስ አንፃር የሚከናወኑ አበይት ተግባራት ናቸው።

2) ከዚህም በተጨማሪ የከተሞች ሳምንት ፋይናንስ ከማንቀሳቀስ አኳያ የሚከተሉትን የባንክ ሂሳብ እና የፋይናንስ አሠራር መርሆዎችን መከተል ይገባል።

ሠ/ የከተሞች ሳምንትን ለማካሄድ ከተለያዩ አካላት የሚሰበሰበውን ገንዘብ ከዚህ በታች በተመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚገለገልበት የባንክ ሒሳብ ቁጥር ገቢ ሆኖ ሥራ ላይ ይውላል::

"በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የከተማ ንፁን ዕዳትና ውበት ማስተባበሪያ ቢሮ ስም በተከፈተው የሒሳብ ቁጥር 1000000985027 ወይም 0171530950600 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ"

ለ/ በዚህ የባንክ ሒሳብ ቁጥር ከላኛው የከተሞች ሳምንት ተራፊ የገንዘብ መጠን እና ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ ከተለያዩ አካላት ለከተሞች ሳምንት ዝግጅት ገቢ የተደረገው ገንዘብ ለእዚሁ ዓላማ ይውላል::

ሐ/ የባንክ ሂሣቡን ለማንቀሳቀስ የሚረዱ የቼክ ጥራዞችን የባንክ ሂሣብ አንቀሳቃሽ በሆኑ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጋራ ፈራሚዎች ለባንኩ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል::

መ/ በየወሩ የባንክ ሂሣብ እንቅስቃሴ መግለጫ ሪፖርት (Bank Statement) ሂሣቡ ከተከፈተበት ባንክ በማምጣት ሂሣቡ ከሚዝገባው ጋር መታረቅ ይኖርበታል (Bank Reconciliation)::

3) የቼክ ፈራሚዎች እደረጃጀት በበጀት አመቱ በስራ ላይ ባለው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አሰራር የፊርማ ውክልና መሰረት የሚፈጸም ይሆናል::

4) የቼክ ጥራዞች አያያዝና የክፍያ አፈጻጸም፣

ሀ/ የከተሞች ሳምንትን ሂሳብ ለማንቀሳቀስ ከባንክ የተሰጡ የቼክ ጥራዞች በእግባቡ መቀመጥ ይገባቸዋል::

ለ/ ለእያንዳንዱ የቼክ ወጪ የክፍያ ማዘዣ መዘጋጀት አለበት::

ሐ/ ቼኮች በሥራ ላይ የሚውሉት በተሰጣቸው የቁጥር ቅደም ተከተል መሠረት ብቻ መሆን አለበት::

መ/ ጉርድ ቼኮችን የያዙ ጥራዞች (ያለቁ ቼኮች) የሂሣብ ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሚመደበው በክፍያና ሂሣብ ማወራረድ ከፍተኛ አፈሰር እጅ ሊቀመጡ ይገባል::

ሠ/ ክፍያ የተፈፀመባቸው የቼክ ቁጥሮችን የያዙ የክፍያ ማዘዣዎች በሂሣብ መዝገብ /IBEX/ ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል::

ረ/ ክፍያ የተፈጸመባቸው ተሳራጅ ቼኮች በአዲተር ሲጠየቁ እንዲቀርቡ ይደረጋል::

5) የገቢ መሞሙ ሂሳብ አያያዝ፣

ሀ/ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ውስጥ የግለሰብ ገንዘብ ገቢ ሊደረግ አይችልም::

ለ/ የክፍያ ቀናቸው ያልደረሰ መይንም ያለፉ ቼኮችን መቀበል አይፈቀድም::

ሐ/ የግለሰብ ቼኮችን መቀበል የሚቻለው ግለሰቡ በባንክ ሂሣቡ ውስጥ ገንዘብ ያለው መሆኑን ባንኩ ሲያረጋግጥ ብቻ ነው:: በሌላ በኩል በCPO መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበን መሞሙ ገቢ ማድረግ ይቻላል::

መ/ በጥሬ ገንዘብ የተሰበሰቡ ገቢዎች በተቻለ መጠን በዕለቱ ባንክ መግባት ይኖርባቸዋል::

ሠ/ ገቢዎችም ሆኑ ወጪዎች በዕለቱ መመዝገብ አለባቸው::

ረ/ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በአግባቡ መቀመጥ ይኖርባቸዋል::

ሰ/ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ተከታታይ ቁጥር ሊኖራቸው ይገባል::

ሸ/ ጥሬ ገንዘብ እንዲይዝ የተመደበው ሰው ገንዘቡን በአግባቡ ስለመቀበሉ፣ ስለማስቀመጡና ስለመክፈሉ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ይሆናል::

ቀ/ ገንዘብ ሰብሳቢውና የሂሣብ መዝገብ የሚይዘው ሰው የተለያየ መሆን ይኖርበታል::

በ/ በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ ሳይቀንስ በዕለቱ ባንክ እንዲገባ መደረግ ይኖርበታል::

ተ/ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ከተሰበሰበ ገቢ ላይ ክፍያ መፈፀም አይቻልም::

ቸ/ በእጅ የሚያዘው ጥሬ ገንዘብ በተቻለ መጠን አነስተኛ ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ/ መሆን ይኖርበታል::

ነ/ የሦስተኛ ወገን መይንም የግል ገንዘብ ከዚህ ሂሣብ ጋር መቀላቀል አይኖርበትም:: ሆኖም የሚኒስቴር መቤቱ የሚያንቀሳቅሳቸው ፕሮጀክቶች ገንዘብ ገቢ ሲደረግ በተቀፅላ ሌጀር መለየት ይኖርበታል::

6) ክፍያን በተመለከተ አጠቃላይ መርሆዎች፣

ሀ/ የክፍያው ምክንያት ምንም ዓይነት ቢሆን ለክፍያው መጎሻ የሚሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ቀርበውና በሚመለከተው ኃላፊ ታይተው ትዕዛዝ ሊሰጥባቸው ይገባል::

ለ/ ማንኛውም ክፍያ እስከ ብር 50,000.00 /ሀምሳ ሺህ/ ድረስ በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንዲሁም ከብር 50 ሺህ በላይ ለሆኑ ክፍያዎች እና ከላይ ለተጠቀሰው የቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሌለበት በአብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም በበላይ አመራሩ መፈቀድ ይኖርበታል::

ሐ/ የክፍያ ግዴታ ከመግባቱ በፊት በቂ የገንዘብ መጠን መኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል::

መ/ የክፍያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መመሪመር ያስፈልጋል፤

- ✓ ክፍያው ተመላሚኝና ለተገዚው ተግባር መሆኑን፤
- ✓ ክፍያውን ያፀደቀው ሰው ውክልና የተሰጠው መሆኑን፤
- ✓ ለክፍያ የሚፈለጉት ሰነዶች በሙሉ የቀረበና ሰነዶቹም ዋና ቅጂዎች መሆናቸውን፤
- ✓ የሂሣብ ስሌቱ ትክክል መሆኑን፤
- ✓ በሕግ የታወቁ ታክሶች መቀነሳቸውን ማረጋገጥ::

ሠ/ ክፍያዎችን በቼክ፣ በባንክ ሂሣብ በዝውውር፣ ወይንም ለጥቃቅን ወጪዎች ከተመደበው ገንዘብ ላይ በጥሬ ገንዘብ መፈፀም ይቻላል::

ረ/ ክፍያዎች የሚፈፀሙት ስማቸው በክፍያ ማዘዣው ላይ ለተጠቀሱት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ብቻ ነው::

7) የገቢና የክፍያ ሰነዶች አጠቃቀም፤

1) ሂሣብ አያያዝን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሒሳብ መዘንብ አያያዝና የገንዘብ ያዥ የአሰራር ሥርዓትን የተከተለ ይሆናል::

2) ወጪዎችና ገቢዎችን ለመመዝገብም ሆነ ገንዘብ ለመቀበልና ክፍያን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች/የገቢና የወጪ ደረሰኞች፤የክፍያ ማዘዣ ቅጾች፤ ወዘተ/ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸው የፋይናንስ ሰነዶች ይሆናሉ::

5. ባህር ዳር የሚተላለፈውን የሥራ ማስኬጃ ሂሣብ በተመለከተ፤

1) ከኤግዚቢሽኑ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎችን ለመሸፈን ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ካለው ሂሣብ ውስጥ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር በዕሁና በሚያሳውቀው የባንክ ሂሣብ ቁጥር የተፈቀደው ገንዘብ ይተላለፋል:: ሆኖም ገንዘቡ ከመላኩ በፊት ዝርዝር ወጪዎቹ በቅድሚያ ቀርበው በአብይ ኮሚቴው መፀደቅ ይኖርባቸዋል::

2) በቅድሚያ ለባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የተፈፀመ ክፍያዎች በፌዴራል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ወጪ ከተደረጉ በኋላ በሚቀርቡት ሕጋዊ የወጪ ማስረጃዎች መሠረት መወራረድ ይኖርባቸዋል::

6. የግዢ መመሪያ መርሆዎች፣

1) 5ኛውን የከተሞች ሳምንት ለማሳካት የሚያስፈልጉ የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥዎችን በተሟላ መልኩ በማቅረብ ሂደት በግዥ አፈጻጸም ቁጠባን መሰረት ያደረገ የአፈጻም ብቃትን እና ውጤታማነትን በሚያረጋግጥ፣ የሚፈለገው የአገልግሎትና የዕቃ ዓይነት ደረጃውን የጠበቀና ፍላጎትን በሚያረካ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሟላት ፕሮግራሙን ማሳካት ይሆናል::

2) የሚከናወነው የግዥ ሂደት የመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብና መመሪያ የተከተለ ሲሆን፣ ፕሮግራሙን በማስፈጸም ረገድ በተቋቋመው አብዪ ወይም የቴክኒክ ኮሚቴ ግዥው ሲፈተድና ሲጸድት የሚከናወን ይሆናል:: በተጨማሪ የሚገዙ የቋሚ ዕቃዎች በጥንቃቄ እንዲያዙና በቀጣይነት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ለቀጣይ ዙር የከተሞች ሳምንት በዓላት አከባበር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ በአግባቡ ተመዝግበው እንዲያዙ ይደረጋል::

3) ፕሮግራሙን ለማሳካት እንዲረዳ የሚያስፈልጉ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥን ለማከናወን በመንግስት የግዥ መመሪያ ላይ በተመለከተው መሰረት የግልጽ ጨረታ፣ የውስን ጨረታ፣ የዋጋ ማቅረቢያ እና ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም የግዥ ዘዴዎችን በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል:: የግዥ ዘዴዎቹ በሥራ ላይ ሲውሉ በመንግስት የግዥ አዋጅና መመሪያ ላይ በተመለከተው የአፈጻጸም ሂደት ይሆናል::

4) ከከተሞች ሳምንት ጋር የተያያዙ ግዥዎችን ለመፈጸም ያስችል ዘንድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሟላት ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ ለኦርጋራመ· ማስፈጸሚያ የሚውል የአገልግሎት·ና የዕቃ ግዥ በሚመለከተው ኃላፊ የጸደቀ የዕቅ ግዢ መጠየቂያ ይቀርባል::

ለ/ በሚቀርበው የዕቃና የአገልግሎት· የግዥ ጥያቄ መሰረት እስከ ብር 1,500 ለሚሆኑ· ግዥዎች በቀጥታ ከዕቃው አቅራቢ መግዛት ይቻላል::

ሐ/ ከብር 1501 በላይ ለሆኑ· የዕቃ ግዥዎች እስከ ብር 100,000 ድረስ፣ ለልዩ ልዩ የአገልግሎት· ግዥዎች እስከ ብር 75,000 ድረስ፣ ቢያንስ ሦስት የዋጋ ማቅረቢያዎችን ከተለያዩ ድርጅቶች እንዲቀርቡ እና እንዲወዳደሩ ይደረጋል::

መ/ ግዥውን ለመፈጸም ተጠቢውን ሰነድ በማዘጋጀት የሚገዛው አገልግሎት ወይም ዕቃ በመንግስት·ን የግዥ እና የፋ·ይናንስ ደንብ መመሪያ መሰረት· ይፈፀማል::

ሠ/ ለሚገዛው አገልግሎት· ወይም ዕቃ በቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ መሰረት· ለነዶቹን በመገምገም አሸናፊውን በመለየት· በግዥ መመሪያው· መሰረት· እንደአስፈላጊነቱ የውሳኔ ሃሳብ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ወይም ለሚመለከተው ኃላፊ በማቅረብና በማጸደቅ ግዥው ከአሸናፊው ድርጅት· እንዲፈጸም ይደረጋል::

ረ/ እንደአስፈላጊነቱ አሸናፊው ድርጅት እቃውን እንዲያቀርብ ውል ይዘጋጃል። በተገባው ውል መሰረት አገልግሎቱ መሰጠቱን ወይም ዕቃው መቅረቡን በሚመለከታቸው የኮሚቴ አባላት ወይም ኃላፊዎች ማረጋገጫ እንዲቀርብ ይደረጋል።

ሰ/ የመንግስት መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በተዘጋጁ ሞያሌዎች ላይ የተገዛው ዕቃ ይመዘገባል።

ሸ/ የተገዛውን ዕቃ ጠያቂው ክፍል በሞያሌ ወጪ በማድረግ ይረከባል፤ ዕቃውም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

ቀ/ የተገዛው ዕቃ ቋሚ ዕቃ ከሆነ የተረከበው አካል በጥንቃቄ በመያዝ ከነፐሮግራሙ ፍጻሜ በኋላ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሞዴል ተመላሽ ያደርጋል።

በ/ የህትመት ፍላጎቶችን መጠንና ይዘት በሚመለከት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ለቴክኒክ ኮሚቴ አቅርቦ ካስወሰነ በኋላ በሚቀርብለት የፍላጎት ዝርዝር መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ይፈጽማል።

ተ/ ለሽልማትና ለልዩ ልዩ ስጦታዎች የሚውሉ የአቅርቦት ፍላጎቶች መጠንና ይዘት በሚመለከት በቴክኒክ ኮሚቴ ተወስኖ በሚቀርብለት የፍላጎት ዝርዝር መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ይፈጽማል።

5) የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት፣

ሀ/ የትራንስፖርት አቅርቦትን በተመለከተ ለነፐሮግራሙ ዝግጅት የሚያስፈልገ የትራንስፖርት ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት የሚሟሉበትን ሁኔታ በዝርዝር በማጥናት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሸከርካሪዎች እንዲሟላ ይደረጋል።

ለ/ የተዘጋጀውን ፕሮግራም ለማስፈጸም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ ተሸከርካሪዎች ለሚፈለገው አገልግሎት ለማቅረብ ካልተቻለ የተሸከርካሪ ፍላጎቶችን በዓይነትና በብዛት በመለየት ለቴክኒክ ኮሚቴው አቅርቦ በማስጸደቅ ከገበያ በኪራይ እንዲሟሉ ይደረጋል። የተሸከርካሪ አገልግሎት በኪራይ ሲሟሉ የመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብና መመሪያን በመከተል ይሆናል።

7. የፋይናንስና የሎጀስቲክስ አቅርቦት ሥራዎች የሚያስተባብር ኮሚቴ፣

5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ዝግጅትን ለማስፈጸም በተዘጋጀው አጠቃላይ አደረጃጀት መሰረት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተውጣጥተው በተዋቀረው መሰረት የሚከተሉት አባላት የያዘ የፋይናንስና የሎጀስቲክስ አቅርቦት ሥራዎችን የሚያስተባብር ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል። የኮሚቴው አወቃቀርም፦

1. አቶ ከበደ ብሩ /ሰብሳቢ/
2. አቶ መንዱ ታከለ /አባልና ም/ሰብሳቢ/
3. አቶ ብዙአየሁ መንበረ/አባል/
4. አቶ አንተነህ በላይ /አባል/
5. አቶ ንጉሴ ተንኮሉ/አባልና ፀሀፊ/ ናቸው።

8. የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች፣

1) የውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም በተመለከተ በዕብይ ወይም በቴክኒክ ኮሚቴው ፀድቆ በሚቀርበው ዝርዝርና የቀን ብዛት መሠረት ክፍያ ይፈፀማል።
2) ለአንድ የከተሞች ሳምንት ተሳታፊ በቀን ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ የውሎ አበል ለሚቆይበት ቀን ተሰልቶ የማይወራረድ ሂሳብ የሚከፈል ሲሆን፣ ይህም አበል የሚቆራረጥ አይሆንም።
3) ፕሮግራሙ በሚካሄድበት ወቅት ለሚካሄዱ የጋናል ውይይቶችና ልዩ ልዩ ዝግጅት ተሳታፊዎች የሻይ እና ቡና እንዲሁም የምሳ ወይም የእራት እንደአስፈላጊነቱ ሆለቱንም በአብይ ኮሚቴ ሲወሰን የመስተንግዶ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።
4) በፕሮግራሙ ላይ ለሚገኙና ሙሉ መስተንግዶና /የምግብና የመኝታ አገልግሎት/ ለሚዘጋጅላቸው አካላት በዕብይ ኮሚቴው ፀድቆ በሚቀርበው ዝርዝርና የቀን ብዛት መሠረት የኪስ ገንዘብ በቀን ብር100.00 /አንድ መቶ ብር/ ይከፈላል።
5) የስልክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት እንደ ስራ ሁኔታ ከየኮሚቴው አባላት ውስጥ ለተለዩት በቴክኒክ ኮሚቴው ሲፈቅድ በቀን፣ በሰው ከብር 50-100 /ከሃምሳ እስከ አንድ መቶ ብር/ድረስ ከአስር ቀን የማይበልጥ ይከፈላል።
6) ለንልበት ሥራ፣ ለቀን ሥራና ለመሳሰሉት ወጪዎች የሚከፈል ገንዘብ በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፀድቀው ሲቀርቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
7) ከከተሞች ሳምንት ሂሣብ ምርመራ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች በአብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወየም በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሲፈቀድ ይፈፀማል። ሆኖም የኮሚቴ ሰብሳቢዎቹ በማይኖሩበት ጊዜ በሚኒስቴር መስርያቤቱ የአሰራር ሥርዓት አግባብ ባለው ኃላፊ ሲፈቀድ ይፈፀማል።

9. የቢሮ ዝግጅት፣

በቴክኒክ ኮሚቴው ለፕሮግራሙ ሥራ ማስተባበሪያ እንዲረዳ የከተሞች ላምንት በሚካሄድበት ባህር ዳር ከተማ ለሚከፈተው ጊዜያዊ ቢሮ በተለያዩ የቋሚ ዕቃዎችና የአላቂ ዕቃዎች እንዲደረጅ ይደረጋል።

1) ለጽ/ቤት ሥራ የሚያስፈልግ የቋሚ ዕቃዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙ ከሆነና የመስሪያ ቤቱን መደበኛ ስራ በማያስተጓጉል መልክ በውሰት በመውሰድ ወይም በጎሉ የሚካሄድበት ከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር እንዲሟሉና በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

2) በግዥ መሟላት የሚገባቸው የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ከሆኑ የግዥ ሃደቱን ተከትሎ እንዲሟሉ ይደረጋል።

10. የመመዝገቢያ ክፍያ፣

1) በ5ኛው የከተሞች ላምንት ኤግዚቢሽን ላይ ቢያንስ ከ120 እስከ 150 ከተሞች ይመዘገባሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የምዝገባው ክፍያ ብር1000 /አንድ ሺህ ብር/ በከተማ ወይም በተሳታፊ ድርጅቱ ይሆናል።

2) የምዝገባ ጊዜውን በተመለከተ ተመዝጋቢ ከተሞች ክፍያቸውን እስከ መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ድረስ ማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ከተሞቹ የሚፈለግባቸውን የምዝገባ ክፍያ በሚከተለው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

" በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የከተማ ኘላን ፅዳትና ውበት ማስተባበሪያ ቢሮ ስም በተከፈተው የባንክ ሒሳብ ቁጥር 1000000985027 ወይም 0171530950600 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ" ይሆናል።

11. የኤግዚብሽን ቦታ /ድንኳን/ ኪራይ አከፋፈል፣

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ከተሞች ላምንት ከህዳር 11 - 17 ቀን 2005 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ይካሄዳል።

1) ለዚህም ከተሞች ለሚያዘጋጁት ኤግዚቢሽን ለድንኳን ኪራይ እና ለመሳለሉት በካሬ ሜትር ብር 150.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ መክፈል ይኖርባቸዋል።

2) የድንኳኖቹም ስፋት ከ12 እስከ 500 ካሬ ሜትር ይሆናል።

3) ከተሞች በካሬ ሜትር የሚፈለግባቸውን ሂሣብ ኤግዚቢሽኑን በሚያሳዩባቸው ቀናት ልክ አስልተው እስከ መስከረም 30 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

12. ከእስፖንሰሮች የሚገኝ ገቢን በተመለከተ፣

ከዚህ ፕሮግራም ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተቋማትና ድርጅቶች በማፈላለግ ለዝግጅቱ የሚሆን ገንዘብ ለሚያሰባስብ በተቋቋመው የስፖንሰር አፈላላጊ ኮሚቴ በኩል በሚቀርብ የቃል ኪዳን ፎርምና ዝርዝር መሰረት ገቢ ይደረጋል፡፡

13. ሂሣብ ማስመርመር፣

1) የከተሞችን ሳምንት ሂሣብ እንቅስቃሴ የተሟላ ሪፖርት በማዘጋጀት ህጋዊ ፈቃድ ባለው የውጪ ኦዲተር እንዲመረመር ይደረጋል፣
2) የከተሞች ሳምንትን አስመልክቶ የተደረገው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ሂሳብ በሶስት ወራት ውስጥ ይዘጋል፡፡
3) የከተሞች ሳምንትን ሂሳብ አስመልክቶ ሂሳቡ ከተዘጋበት ቀጥሎ በሚገኙት ሶስት ወራት ውስጥ በኦዲተሮች ምርመራው ተጠናቆ ውጤቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

14. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ፣

ይህ መመሪያ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር ቀርቦ ከጸደቀበት ከ ፋጉሜን 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ የ5ኛው የከተሞች ሳምንት ሂሳብ ተመርምሮ እስከሚዘጋበት ድረስ በስራ ላይ ይውላል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር